# ፊማ እና የፊንፊኔ መንግሥት፤ ተጻራሪ ገጽታዎች

## መግቢያ፣

የጽሑፉ ርእስ ፊማ የተወሰደው ከአሜሪካ የፌደራል ድንገተኛ አደጋዎች ማስተባበሪያ ኤጀንሲ ምሕጻረ ቃል ነው፤ FEMA (Federal Emergency Management Agency) እንዲል በሙሉ ንባቡ፡፡

## መነሻ፤

የዚህ ጽሑፍ ማጠንጠኛ ኃይለ ሃሰብ ሻለቃ ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ ከኢሳቱ (እሳቱ ልበል ይሆን?) ሲሳይ አጌና ጋር ያደረጉት ቃለ ምለልስ ነው፡፡ በዚያ ውይይት ከተነሱት አንኳር ነጥቦች አንዱ የኢትዮጵያ የቸነፈርና የችጋር አዙሪት ሲሆን ሻለቃው አስከፊውን የ1977ዓ.ም የረሃብ እልቂት ከሙሉ ጥፋቱ ለመታደግ በዕማማኮ (የዕርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን) በኩል የተደረገውን ከፍ ያለ ጥረትና እነ ማይክል ጃክሰን ፣ ቦብ ጊዶልፍና የምዕራባውያን የኪነጥበብ ባለሞያዎች ያደረጉትን ፍጹም የሆነ ሰብአዊ ውለታ ያስታወሱበት ነው፡፡ አያይዘውም ራስ ሳይጠና ጉተና በሚለው ዘይቤ አቅሙን የማያውቀው ሕወሃት መራሹ መንግሥት ለአፍሪካ አገራት ሳይቀር መልካም ተሞክሮ ለመሆን የበቃውን ዕማማኮ ለመዘከር እንኳን እንዳይበቃ አድርጎ ያፈራረሰበትን እኩይ ተግባር ከራሳቸው ተሞክሮ ቀንጭበው ለማካፈል ችለዋል፡፡ የመንግሥቱ ኃይለማርያምን ሶሺያሊዝም (አብዮቱ) ኢትዮጵያን እንዴት እንዳለመለማት የደነፋበትን የስድስት ሰዓት ንግግር በማስታወስ የዛሬዎቹ መንግሥቱ ኃለማርያሞች የእድገትና የመካከለኛ ገቢ ፉከራ ጭራና ቀንዱ ሳይቀር ከደርግ የተኮረጀ መሆኑ የተጋለጠበት አቀራረብ እንደነበር ቪዲዮውን በመመልከት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

**የእኔ እይታ፣**

1977ዓ.ም የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ነበርኩ፡፡ በመቅሰፍታዊው ረሃብ የተጠቃውን የሰሜኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከእልቂት ለመታደግ ዕማማኮ እንደ ታላቁ የዓባይ ወንዝ በኮንቮይ ስምሪት ወደ ወለጋ ሲያፈልሳቸው መመልከት የዕለት ተዕለት ዘግናኝ ትርኢት ነበር፡፡ ወገኖቼ የሚበሉት፣ የሚጠጡት፣ የሚለብሱት አጥተው ተራቁተው "ከሰው ተራ ወጥተው አጥንት ተራ"[1] ገብተው ማየት አስጨናቂ ነበር፡፡ በዚህ አገር አቀፍ ክስተት አዲስ አበባ የአመጋገብ ሥርዓት ለውጥ እንዳደረገችም ሲነገር ለማድመጥ ችያለሁ (የጉራጌ ብቻ የነበረው ቆጮና ተዘማጅ ውጤቱ ይጠቀሳል)፡፡ የዚህ ሰቅጣጭ ክሰተት ሁሉት አበይት እውነታዎችን እንዳስተውልና እንድጠይቅም ያደርገኛል፡፡ እናም ሁሌም ራሴን እጠይቃለሁ፡፡

1. የ "We Are the World" አዘጋጆች በተለይም ደግሞ ማይክል ጃክሰንና ጓደኞቹ ለእኔ እንደ ሰማያዊ የምሕረት መልእክተኞች ናቸው፡፡ እነዚህ ባለውለታዎችንን የሚያስታውስና ኢትዮጵያውያንን በቁጭት በኩል ወደ ልማትና ከእንግዲህ አልሸነፍም ባይነት ታሪክ የሚያደርስ መታሰቢያ ለማቆም ለምንን ተሳነን?
2. ሚሊዮኖች ከሰሜኑ የአገራችን ክፍል በዚያ ችግር ሲፈልሱ የኦሮሞ፣የጋምቤላና የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ኢትዮጵያዊ እንግዳ ተቀባይነታቸው የተፈጠሩበት ባሕርያቸው መሆኑን ያስመሰከሩበት እንደመሆኑ መጠን እንዴት የእነዚህን ሕዝቦች ታላቅነት የሚያሳይ መታሰቢያ ለማቆም ተሳነን?

[1] የክበበው ገዳን ቀልድ ያስታውሷል፡፡

*(የአኖሌ ሐውልት የኦሮሞ ሕዝብ መገለጫ ሆኖ ማየት ምንኛ አዛሳኝ ነው፡፡ በቸነፈር ረሃብ የመገበ፣ ጉዲፈቻን ያህል ታላቅ ባሕል ለዓለም ያበረከተ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ኦሮሞ፣ ለምነቱ የሚመግበን፣ ደግነቱ የሚያኖረን ጋምቤላ፣ ምግቡ፣ አልባሳቱ፣ ጭፈራው የሚያደምቀን ደቡብ በእርግጥ የኢትዮጵያዊነት ጠላት ሆኖ መቅረቡ እውነት የሕዝቡ ነው?)*

**መለስ ወደ ቤተ መንግሥት እንደ ገባ መጀመሪያ ያደረገው ለአቅም ግንባታ ሥልጠና ከእንግሊዙ ኦፐን ዩኒቨርሲቲ ኦፐን ቢዝነስ (Open Univesity Open Business School) ስኩል የርቀት የማኔጅመንት ትምህርት መጀመር ነበር፡፡ በዚህ የሥልጠና ሥርዓት ሁሉም ከፍተኛ አመራሮች አልፈዋል፡፡ ወጪው የተሸፈነውም በዩንዲፒ (UNDP) ነው፡፡ የሥልጠናው የመጀመሪያ ዓመት ኮርስ ሠርቲፊኬት የሚያስገኝ ሲሆን የመማሪያ ማጻሕፍቱ መሪ ቃል "The Capable Manager" የሚል ነበር፡፡**

**በዚህ የጀመረው የመለስና ጓደኞቹ ትምህርት አንዳንዶቹን ዛሬ ዶክተር ለመሰኘት አብቅቷቸዋል፡፡ የትምህርትን መልካምነት የሚጠላ የለምና የእነርሱ መራቀቅ የሚመሰገን ቢሆንም በገበዩት እውቀትና በተግባራቸው መካከል ያለው ተቃርኖ እጅግ ሰፊ መሆኑ ደግሞ "ትምህርት ለጥፋት?" የሚል ጥያቄ እንድናነሳ ይገፋፋል፡፡ ለዚህ ጥሩ ዋቢ የሚሆነው ዕማማኮ ነው፡፡ በቸነፈርና በችጋር አዙሪት ለምትወዘወዘው ኢትዮጵያ ጠንካራ መሠረት የነበረውን ዕማማኮ ድራሹን በማጥፋት "The Destructive Manager" ያሚያሰኝ ተግባር መፈጸሙ እውነት ነው፡፡[2]**

**በዕማማኮ መቃብር ላይ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ብለው ያቋቋሙት ይስሙሌ ተቋማቸው እንኳን ዛሬ የለም፡፡ አሥራ ሚሊዮኖች ተርበው እነርሱን ለማቋቋም፣ ለመደገፍ፣ ለመመገብ፣ ለማስፈር የሚችል ተቋም የለም፡፡ የዚህን ተቋም ግዙፍነት ለመረዳት ሩቅ መሄድ አያስፈልግም በመቶዎች ወይም በአንድ ሺዎች የሚቆጠሩ አትሌቶችን የሚመሩ እንደ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን፣ እንደ ቴኒስ ፌዴሬሽን፣ እንደ ዳርት ፌዴሬሽኖች ያሉ ተቋማት ሕልው ሆነው በሚተነፍሱበት አገር ዕማማኮን የሚመስል ተቋም አለመኖር ከቀልድም በላይ ስላቅ ነው፡፡ ደን ልማት ሚኒስቴርን አጥፍቶ ደን ማልማት ብሎ ፉገራ፣ የአበባ ኤክስፖርት ብሎ ለሙን የኢትዮጵያ መሬት በአደገኛ ኬሚካል ለምንም ነገር እንዳይሆን መበከል ሌላ ምን ይባላል ያው "የባለ ራእዩ መሪያችንና የሕዳሴያችን" ትሩፋት ነው ብለን ከመደስኮር ውጪ፡፡**

**በእርግጥ፤ የዓለም አቀፍ ልምድ የሕወሃት መራሹን ደንባዣ መርህ ያንፀባርቅ ይሆን? እስኪ የልዕለ ኃያሏ አሜሪካንን ጓዳ በጥቂቱ እንግለጠውና አሜሪካ ለአደጋ ጊዜ ያላት ግንዛቤና ዝግጅነት ምን እንደሚመስል ቀጥሎ እንመልከት፡፡**

## Federal Emergency Management Agency (FEMA)

**የአሜሪካ የፌደራል ድንገተኛ አደጋዎች ማስተባበሪያ ኤጀንሲ ከ37 ዓመታት በፊት በጂሚ ካርተር ፕሬዚዳንታዊ ትዕዛዝ የተቋቋመ ድርጅት ነው፡፡ በ2003ዓ.ም ከአሜሪካ የግዛት አስተዳደር መሥሪያ ቤት ሥር እንዲሆን እስከተደረገበት ጊዜ በተናጠል ሲሠራ ቆይቷል፡፡ ይህ መሥሪያ ቤት ጥንተ ትረካውና ጽንሰ ጥንሰሱ በ1803ዓ.ም (እ.አ.አ) በኒው ሐምሻየር ግዛት ውስጥ በአንድ ከተማ የደረሰውን የቋያ እሳት አደጋ**

[2] በነገራችን ላይ የደንና ዱር አራዊት ጥበቃ ሚኒስቴር /ባለሥልጣን መሥሪያ ቤትን በማፍረስም በኢትዮጵያ የደን ሃብት ጥፋት ላይ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ አሜሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ የገባችሁ ኢትዮጵያውያን አውሮፕላኑ ለማረፍ ሲያኮበኩብ አስተውላችሁ ከሆነ አሜሪካ ዓለምን የምትመራው እንደ ወንበዴ ጥቅጥቅ ባለ ደን ውስጥ ተደብቃ ነው'ዴ ሳያሰኛችሁ እንዳልቀረ እገምታለሁ፡፡

ከመከላከል ጋር በተያያዘ የአሜሪካ ኮንግረስ የኮንግረስ ደንብ (Congress Act of 1803) በማለት ካወጣው የመጀመሪያ ደንብ ጋር ይሰናሰላል፡፡

መሥሪያ ቤቱ ግልጽ ተልእኮና ርእይ አንግቦ ለተፈጻሚነታቸው የሚሠራ ነው፡፡

ተልእኮው በአጭሩ፣

እንደ አገር የሚገጥሙንን አደጋዎች ሁሉ ለመመከት፣ለመጋፈጥ እና ከሚደርሱብን አደጋዎች ለማገገም የሚያስችለንን ዘላቂ አቅም በመገንባትና በሂደትም በማሻሻል ዜጎችንና የአደጋው ተጠቂዎችን መርዳት፣ የሚል ግርድፍ ትርጉም ያለው ሲሆን፤

የኤጀንሲው ርእይ በአንጻሩ ከሦስት ቃላት የተቀመረ ነው፤

ዝግጁ ሃገር "A Nation Prepared" ይላል፡፡

ኤጀንሲው ከ15,000 በላይ ሠራተኞች የሚርመሰመሱበት ግዙፍ የዝግጁነት ተቋም ነው፡፡ ከአደጋ ጊዜ ደራሽነት እሳቤ አንጻር የተቀመረው ድርጅታዊ መዋቅር አሥር ክልላዊ ጽ/ቤቶችን (Regional Offices) የያዘ ሲሆን የተፈቀደ ዓመታዊ በጀቱ ከ10 ቢሊዮን ዶላር በላይ ይደርሳል፡፡ ኤጀንሲው ቅድመ መከላከል ከሚያደርጋቸው ተግባራት በተጨማሪ ድኅረ ቀውስ ዜጎችን ወደቀደመ የኑሮ አቋም ለመመለስ በሚደረገው እርዳታና ድጋፍ እንዲሁም ልዩ ልዩ ሥልጠናዎች ከፍተኛ ወጪዎችን ያደርጋል፡፡ የዜጎች ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ስነ ልቦናዊ እክሎች መፍትሔ እንዲያገኙ መሥራት የሕልውናው ዋና ምክንያት ነው፡፡ አሜሪካ የዚህን ተቋም አስፈላጊነት ለመገንዘብ ከዛሬ 213 ዓመታት በፊት የገጠማት የቃጠሎ ውድመት ከበቂ በላይ ተሞክሮ ሆኖ ኮንግረስ የዛሬውን ግዙፍ ተቋም የመሠረት ድንጋይ የጣለው በዚያ ጊዜ ባወጣው ቃጠሎን የተንተራሰ ደንብ መሆኑ በእጅጉ ሊሠመርበት የሚገባ አርቆ አሳቢነት ነው፡፡

ከዚህ የአሜሪካ ተቋም ወጥተን የአገራችንን ጉዳይ ጥቂት በንጽጽር እንይ፡፡ እንደ መልካም እድል ሆኖ ከአደጋዎች ሁሉ ረሃብና ቸነፈር የኢትዮጵያ ወዳጆች ናቸው፡፡ ለረሃብ ስንዴና ዘይት ካለ ለጊዜው በቂ ነው፡፡ የተፈጥሮ አደጋ ግን ይሄ ብቻ አይደለም፡፡ በአንድ በኩል የመሬት መንቀጥቀጥ፣ መንሸራተት፣ናዳ፣ መጥለቅለቅ፣ እሳተ ገሞራ፣ እሳት፣ወረርሽን፣ በሌላ በኩል ጦርነት፣የጎሳ ግጭት፣ድንበር ዘለል ዘረፋና ንጥቂያ ሰው ሰራሽ አደጋዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ አደጋዎች ውስጥ ከፍተኛ ቀውስ ያሰከተለ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ እሳተ ገሞራ፣ ናዳና መንሸራተት እስከ አሁን ያልገጠመን ቢሆንም ሌሎቹ አደጋዎች በተለይም ረሃብና የጦርነት ቀውስ በየዘመናቱ ተፈራርቀውብናል፡፡ እንደ ዜጋ መንግሥታት ሚሊዮኖችንና መቶ ሺህዎችን ቀርቶ ጥቂት የኅብረተሰብ ክፍሎችንም የማቋቋምና የመርዳት የሞራልና የሕግ ተጠያቂነት አለባቸው፡፡

አገራችን ጠንከር ያለ አደጋ ቢገጥማት ምላሹ ከየት ነው የሚገኘው፣ የትኛውስ ተቋም ነው የመከላከል ጡንቻ ያፈረጠመው፡፡ በተለይም ከረሃብ ውጪ ያሉት አደጋዎች በከተሜው ነዋሪ ላይ ቢደቀኑ ጥፋቱ ሁለቸዮሽ ከመሆን አያመልጥም፡፡ የከተማ ነዋሪ መሠረታዊ ፍላጎት በስንዴና በዘይት ብቻ ይቆማል ብሎ ማሰብ ዘበት ነው፡፡ የውሃ፣ የመብራት፣ የንጽሕና መጠበቂያ፣ አልባሳትና መጫሚያዎች፣ ኮሚውኒኬሽን ሁሉ ወጥረው የሚያስጨንቁ ጥያቄዎች ይሆናሉ፡፡

**የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ሥራ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ የሚዳፈን የሚመስላቸው መሪዎቻችን ቢሊዮን ዶላሮችን ከሚመጸውቱላቸው እነ አሜሪካ ምንም ምክር አለማግኘታቸው ወይም አግኝተው ችላ ማለታቸው ወይም ዕማማኮን የሚመስል ተቋም ማቋቋም ደርግን ማስታወስ ነው ብለው በቸከው ሃልዮት ተሸንፈውም ከሆነ በሁለቱም ምክንያት 90 ሚሊዮን ሕዝብ ያላት አገር እንደ ዋዛ ስትጠፋ ማየት የሚያስደስታቸው ከሆነ ምን ዓይነት ፊልም እያዩ ቢመስላቸው ይሆን ብለን እንድንጠይቅ ያስገድዳል።**

**መሠረታዊ ችግራችን ተቋሙን መገንባትና ማፍረስ አይደለም። ያ ተግ4ባር ነው፤ መቅደም ያለበት እየተከተለ አስቸገረን እንጂ። ዛሬ ዓለም የጎጆ ቤቶች ስብስብ መስላ በተሳሰረችበት የቴክኖሎጂ ዘመን እውቀትን መገብየት፣ ካልሆነም መቅዳት ከባድ ባልሆነበት ዘመን አሜሪካኖቹ ከ213ዓመታት በፊት የነበራቸውን የአእምሮ ልቀት ማግኘት አለመቻላችን በሁሉም ዘርፍ እየጎዳን ይገኛል። Critical thinking (ጥሞና) የላዳበረ መሪና ምሑር እንዴት መፍትሔ ሊያመነጭ ይችላል።**

**ለመሆኑ እንዲህ ዓይነት ተቋም ያስፈልገናል? ሕወሃት መራሹ ኢሕአዴግም ሆነ በጎ ብልሃት ያለው ዜጋ ሁሉ ሊመክርበት የሚገባ ጉዳይ ነው፤ ነገ እነዚህ አደጋዎች በሁለትና ሦስት እጅ ልቀው መከሰታቸው የሚቀር አይመስልምና።**

**ተስፋዬ**

**ማጣቀሻዎች፣**


FEMA. የተወሰደ ከ http://www.fema.gov

https://www.fema.gov/pdf/about/budget/fema_fy2013_bib.pdf

Esat Tube. ESAT Bezhi Samint Major Dawit Weldgiorgis May 8 2016. http://video.ethsat.com/?p=23668